# ተዋቸው ይሂዱ !

ተዋቸው ይሂዱ ፤ ተነግረው ካልሰሙ
መማር ተስኗቸው ፤ ታሪክ ከደገሙ
አትዘኑላቸው ፤ ዛሬም ካልታረሙ
ከወያኔ ጋራ ፤ ይግቡና ያዝግሙ
ውሃ መውቀጥ አይሁን ፤ ከንቱ ነው መድከሙ ።

ስትመክረው ፣ ስትነግረው ፤ ጆሮ ዳባ ካለ
የሳት እራት ሊሆን ፤ ከተንከለከለ
ወዳጁን ወደጎን ፤ ገፍቶ ካገለለ
ከጠላቱ ማዕድ ፤ ገብቶ ከተዶለ
መከራ ይምከረው ፤ ወዶ ነው ምናለ
አይታዘንለት ፤ በተንዘላዘለ ።

ህዝብን ካስቀየመ ፤ በትዕቢት ተነፋቶ
አንቱ ይባል እስቲ ፤ ከወደደው ገብቶ
ፋይዳ እማይሰራበት ፤ አንገቱ ተደፍቶ
እያጨበጨበ ፤ ይኑር ሆዱን ሞልቶ
ባመፅ አኪወጣ ፤ በጉልበት ተገፍቶ
ውርደት ተከናንቦ ፤ ጋማው ተጎትቶ ።

የልባቸው ይሙላ ፤ ተዋቸው ይሂዱ
ከነ አሀዮ ተራ ፤ ገብተው ይማገዱ
ይንከባለሉበት ፤ ይድላቸው አመዱ
ከቢጤያቸው ጋራ ፤ ገብተው ይላመዱ
ከጓጉለት ስልጣን ፤ ነገ እስከሚወርዱ
ክብራቸው ተገፎ ፤ እስከሚዋረዱ
ተዋቸው ይሂዱ !
ትግል አሽመድምደው ፤ ባገር ቢቀልዱ
ለነገ ውርደት ነው ፤ ለዛሬ ቢከዱ
በህዝብ ዳኝነት ፤ እስከሚፈረዱ
እንደ ማገዶ እንጨት ፤ ከስለው እስኪነዱ ።

ታዛቢው
February 07/2010